የሰ/መ/ቁ. 28802

ታህሣሥ 8/2000

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ ሐጎስ ወልዱ

ወ/ት ሒሩት መለሠ

አቶ ታፈሰ ይርጋ

**አመልካች፡-** እነ ወ/ሮ በየነች ይገዙ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ሳሙኤል ዝቅአርጋቸው - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት በሐራጅ ተሸጦ ግራ ቀኙ እንደየድርሻቸው ይከፋፈሉ በማለት በበታች ፍ/ቤቶች በመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካችኞች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካቾች ላይ ባቀረቡት ክስ ከሟች አባታቸው በውርስ ተከፍሎ የሚደርሳቸውን በወረዳ 16 ቀበሌ 09 ክልል የሚገኘው ቁጥር 249 የሆነው ቤት የዋጋ ግምቱ ብር 120 ሺህ ሲሆን ከዚህ ላይ የከሳሽ ድርሻ 1/6ኛ ብር 20.000 /ሃያ ሺህ/ ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ ተከሣሾች እንዲከፍሉኝ እንደዚሁም ሟች አባቴ ከሞቱበት ጥቅምት 1992 ዓ.ም. ጀምሮ ቤቱን ተከሣሾች ይዘው ለተጠቀሙበት ብር 2186.87 ጨምሮ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የከሳሽ ክስና ማስረጃም ለተከሳሾች ደርሶ በሰጡት መልስ ከሳሽ የሟች አቶ ዝቅአርጋቸው ተካ ልጅ መሆኑን አምነው የቤቱን ግምት ለከሳሽ በድርሻው ልክ ለመስጠት እንደዚሁም የኪራይ ክፍያ ጥያቄውን በተመለከተም ለመክፈል ፈቃደኛ

እንደሆኑ በመግለጽ መልስ ሠጥተዋል፡፡ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም የተጠቀሰው ቤት በመሐንዲስ ተገምቶ በተገኘው ግምት ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥና የከሳሽ ድርሻም ከተጠየቀው የኪራይ ክፍያ ጋር እንዲከፈላቸው በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ተከሣሾች በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

ይህም ችሎት አመልካቾችና ተጠሪ የቀረቡትን ክርክር መርምሯል፡፡

ሊፈታ የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በመሐንዲስ ተገምቶ በተገኘው ግምት በሐራጅ ተሸጦ የተጠሪ ድርሻ ይከፈል ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ አግባብነቱን በተመለከተው ነው፡፡

በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁን ተጠሪ ዳኝነት የጠየቁት ከላይ እንደተመለከተው ከአባታቸው በውርስ የተላለፈው የጋራ የውርስ ቤት ግምቱ ብር 120,000 /አንድ መቶ ሃያ ሺህ/ መሆኑን ገልጸው ከዚህ ላይ ድርሻዬ ነው የሚሉት ብር 20,000 /ሃያ ሺህ/ ይክፈለኝ በማለት ነው፡፡ ተከሣሾች የአሁን አመልካቾችም በክስ በተጠየቀው መሠረት ገንዘቡን ለመስጠት ፈቃደኞች መሆናቸውን ገልጸው መልስ ሠጥተዋል፡፡

ከሣሽ ዳኝነት የጠየቁትና የተከሳሾችም መልስ ከላይ የተለከተው ከሆነ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ዳኝነት በተጠየቀውና በታመነውም መሠረት ይህንኑ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ተከሳሾች ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሣኔ መስጠት ሲገባው ከዚህ አልፎ ቤቱ በመሀንዲስ ተገምቶ በሐራጅ ተሾጦ የከሳሽ ድርሻ ይከፈላቸው በማለት ውሣኔ መስጠቱ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 182/2/ ጋር ያልተጣጣመና ባልተጠየቀ ነገር ላይ የተሰጠ ዳኝነት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የፌዴራል ከ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ በአግባቡ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ቀጥሎ የተለከተው ተወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 15166 በ21/3/97 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37786 በ20/3/99 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ዳኝነት በጠየቁት መሠረት ብር 20,000 /ሃያ ሺህ/ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ከሚታሰብ 9% /ዘጠኝ በመቶ/ ወለድ ጋር አመልካቾች እንዲከፍሏቸው ተወስኗል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ